# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የድጋፍ ማዕቀፎች አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ክፍል አንድ ........................................................................................................................1

*መግቢያ*..............................................................................................................................*1*

*የኤጀንሲ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር*..................................................................................*2*

ዓላማ ..............................................................................................................................2

ሥልጣንና ተግባር ................................................................................................................2

*ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል*..................................................................................*3*

*የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ* ............................................................................................*4*

*የኦዲቱ ዓላማ* ..................................................................................................................*4*

*የኦዲት አካባቢ (Audit Area)*............................................................................................*4*

*የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) እና የመመዘኛ መስፈርት* ......................................*4*

*የኦዲት ወሰን*...................................................................................................................*5*

*የኦዲት ዘዴ*......................................................................................................................*6*

*የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process Description)* ...............................................................*6*

ክፍል ሁለት......................................................................................................................7

ግኝቶች ...........................................................................................................................7

የፋይናንስ ብድር አቅርቦት እና አመላለስ አፈጻጸምን በተመለከተ...............................................7

የብድር ዋስትና ፈንድ በተመለከተ .......................................................................................10

የድህረ ብድር ድጋፍና ክትትልን በተመለከተ ........................................................................12

የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት አቅርቦትን በተመለከተ ..........................................................13

የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት መሰረተ ልማት የተሟላላቸው መሆኑንን በተመለከተ .................14

ኢንተርፕራይዞች ደረጃ ዕድገት ሽግግርን በተመለከተ ............................................................16

ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ኢንተርፕራይዞችን በተመለከተ .....................18

የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የፊትና የኋላ የገበያ ትስስርና ቁርኝት በተመለከተ ..........19

የማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት መጠቀሚያ የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ...................20

ኢንተርፕራይዞች በማዕከላቱ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜን በተመለከተ .......................................21

የማዕከል የቆይታ ጊዜ ጨርሰው ለሚወጡ ኢንተርፕራይዞች ስለሚደረግ ድጋፍ በተመለከተ ........22

ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በሚመለከታቸው አካላት መካከል ያለ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ....23

ክፍል ሦስት....25

መደምደሚያ....25

ክፍል አራት....27

የማሻሻያ ሃሳቦች....27

አባሪ 1. የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ አደረጃጀት....30

አባሪ.2 የኦዲት መመዘኛ መስፈርት....31

አባሪ 3. የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process Description)....35

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ እንደ ተቋም ከተመሰረተ ግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ዕድሜን አስቆጥሯል፡፡ ከአመሰራረቱ አንስቶም በተለያዩ ስያሜዎች ሲጠራ ቆይቷል፡፡
2. በ1934 ዓ.ም የግርማዊት እቴጌ መነን እጅ ጥበብ ትምህርት ቤት በሚል ተመሰረተ፡፡ በ1969 ዓ.ም የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና ዕደትበባት ማስፋፊያ ድረጅት /አዕማድ/ ተብሎ እንደገና ተቋቋመ፡፡
3. ከ1984 ዓ.ም የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና ዕደ-ጥበባት ልማት ማስፋፊያ ድረጅት /አዕልማድ/ የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ድርጅታዊ አቋሙ በወቅቱ ለአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍና በሚያመች መልኩ ተደራጅቶ እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ ሲሰራ ነበር፡፡
4. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት በሀገራችን የኢኮኖሚ ልማት ዕድገት ውስጥ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ዘፍር ሊያበረክት የሚችለውን ከፍተኛ አስተዋፅዎ በመገንዘብ ቀደም ሲል ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስተር ተብሎ ሲጠራ የነበረው መ/ቤት የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ስራ ድርጅት ልማት ስትራቴጂ በማውጣት የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ስራዎች ልማት ድረጅት በሚል ስያሜ በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ቁጥር 33/1990 እንዲቋቋም ተደረገ፡፡
5. በዚህ መሰረት ለረዥም ዘመናት ዕደጥበባትና የጎጆ ኢንዱስትሪ እየተባሉ የቆዩት ተቋማት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝነት የታወቁት ከ1990 ዓ.ም ወዲህ ሲሆን፡፡
6. መንግስት ለዘርፉ ልማት የሰጠው ትኩረት እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ከዘርፉ ልማት ቀደም ሲል የተገኙ ልምዶችንና ችግሮችን በመለየት እንዲሁም ከውጪ ሀገሮች የተቀሰሙ ምርጥ ተሞክሮዎችን መሰረት በማድረግ ይህ ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 201/2003 ዓ.ም የማቋቋሚያ ደንብ መሰረት የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በሚል ስያሜ በአዲስ መልክ ተቋቋመ፡፡

## የኤጀንሲ ዓላማ፤ ሥልጣንና ተግባር

### ዓላማ

7. የኤጅንሲው ዓላማዎች፡-

- የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ተወዳዳሪ፤ ቀጣይነት ያለውና ለኢንዱስትሪው ልማት ጠንካራ መሰረት የሚጥል እንዲሆን ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማትን መደገፍና ማስተባበር፤
- ሰፊ የስራ ዕድል እንዲፈጠርና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ የተሰማሩትን የህብረተሰብ ክፍሎች ገቢ በማሻሻል ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ገቢ በማሻሻል ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ማድረግ፡፡

ናቸው፡፡

### ሥልጣንና ተግባር

8. ኤጅንሲው ደንብ ቁጥር 201/2003 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

- የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ለማፋጠን የሚረዱ ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፤ መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃል፤ ሲፈቀደም አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡
- የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ የድጋፍ ማዕቀፎች እንዲቀረጹ ያስተባብብራል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
- የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትና ተወዳዳሪነት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት መፍትሔ ይሰጣል፤
- የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የሚደግፉና የሚያስተባብሩ የክልል ተቋማትን የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤
- የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍን ስትራቴጂ መሰረት በማድረግ የዘርፉን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፡ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን የዕሴት ሰንሰለት መሰረት በማድረግ የጥቃቀንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት በጥቃቅንና

አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የስልጠና የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ያስተባብራል፣

- ምርጥ ተሞክሮዎችን በማጥናት በመቀመርና በማሰራጨት የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ያግዛል፣
- የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በዘርፎቻቸው በማህበር እንዲደራጁ በመደገፍ ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደግፋል፣
- ለጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፣
- ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የግልና የመንግስት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን ያስተባብራል፣
- የንብረት ባለቤት ይሆናል ውል ይዋዋላል በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

9. የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሥር በአንድ (1) ዋና ዳይሬክተር፣ በሦስት (3) ም/ዋና ዳይሬክተር፣ በአስር (10) ወሳኝ የስራ ሂደቶች እና በአምስት (5) ደጋፊ የስራ ሂደቶች የተዋቀረ ሲሆን፡፡ ዋና ዳይሬክተሩ አጠቃላይ በፖሊሲና እስትራቴጂክ አካሄድ ላይ ተመስርቶ በበላይነት የመምራት፣ የማቀናጀት፣ የማስተባበርና የመቆጣጠር ተግባር ይዞ ለሁሉም የስራ ሂደት ባለቤቶች ሙሉ የሥልጣን ውክልና በመስጠት ሥራው በማከናውን ይገኛል፡፡
10. እስከ ጥር 2008 ዓ.ም ድረስ የኤንሲው የሰው ኃይል ሲገልጽ በትምህርት ደረጃ ሲተነተን ሁለተኛ ድግሪ 13፣ መጀመሪያ ድግሪ 83፣ ዲፕሎማ 66፣ ሰርተፍኬት 6፣ 12ኛ እና ከ12ኛ ክፍል በታች 124፣ የመንግስት ሹመኞች 4 ሰራተኞች ሲሆኑ በፆታ ሲገለፅ ወንድ 156 ሴት 128 ናቸው፡፡

11. የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር (አባሪ 1) በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡

## የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ

12. የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ስራውን የሚያከናውነው ከመንግስት በሚመደብለት በጀት ሲሆን በ2004፣ 2005፣ 2006 እና 2007 በጀት ዓመታት እንደ የቅደም ተከተሉ የተመደበለት መደበኛና ካፒታል በጀት ብር 16,752,301፣ ብር 27,706,330፣ ብር 35,018,300 እና ብር 50,680,200 ሲሆን ከዚህ ውስጥ በ2004 በጀት ዓመት ብር 14,574,540፣ በ2005 በጀት ዓመት ብር 25,517,504፣ በ2006 በጀት ዓመት ብር 29,495,243 እንዲሁም በ2007 በጀት ዓመት ደግሞ ብር 48,436,705 ስራ ላይ አውሏል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

13. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጠውን የድጋፍ ማዕቀፎች አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ማከናወኑንና ውጤታማ መሆኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ ችግሮች ካሉ በመለየት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የአሰራር ግድፈቶችን ለማስተካከል የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳብ ለመስጠት ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

14. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ***"የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የድጋፍ ማዕቀፎች አፈጻጸምን በተመለከተ የተዘረጋው የአሠራር ስርዓት በቁጠባ፤ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑን መገምገም"*** የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) እና የመመዘኛ መስፈርት

### የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ

15. ከላይ በተገለጸው የኢዲት አካባቢ ሥር ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተመርጠዋል፡፡ እነሱም፡-

1. የፋይናንስና ብድር አቅርቦት ድጋፍ ተግባር በቁጠባ፣ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፡፡
2. የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ድጋፍ አተገግባር በቁጠባ፣ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፣
3. የፋይናንስ፣ ብድር አቅርቦት፣ የማምረቻ እና የመሸጫ ማዕከላት የድጋፍ አተግባር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊያሠሩ የሚያስችል ውጤታማ የአሠራር ሥርዓት ተዘረጋ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉ ናቸው፡፡

**የኦዲት መመዘኛ መስፈርት**

16. ከላይ የተመረጡትን ሦስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 24 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የመንግስት አዋጆች፣ የኤጀንሲው መተዳደሪያ ደንብ፣ የሥራ መመሪያ እና በኤጀንሲው የተጠናው መሰረታዊ የስራ ሒደት ለውጥ ጥናት፣ የድጋፍ ማዕቀፎች የአሰራር ስርዓት መመሪያ፣ መልካም ተሞክሮዎች፣ የሥራ አመራር ቃለ ጉባኤዎች እና የዳሬክተሮች ቦርድ ቃለ ጉባኤዎችን ሲሆኑ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ ሥራው የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) **በአባሪ 2** ተያይዟል፡፡

## የኦዲት ወሰን

17. ዝርዝር ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2004 የበጀት ዓመት እስከ 2007 በጀት ዓመት ድረስ ያለውን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የድጋፍ ማዕቀፎች አፈጻጸምን በተመለከተ የተዘረጋው የአሠራር ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ ስለመሆኑን መገምገም ሲሆን ኦዲቱ በዋነኛነት የሚከናወነው የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ዋና መስሪያ ቤት፣

በሦስት ክልሎች፤ የዞንና የወረዳ ኤጀንሲ ጽ/ቤቶች፤ መንግስት ልዩ ትኩረት በሰጣቸው በናሙና በተመረጡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ፈፃሚ ባለ ድርሻ አካላትን በማካተት መረጃዎችንና ዶክመንት በመከለስ፤ መጠይቅ በማቅረብ እና በአካል ተገኝቶ የኢንተርፕራይዞቹን ሁኔታ በመገምገም ተከናውኗል፡፡

## የኦዲት ዘዴ

18. ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የኤጀንሲው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር መጠይቅ በማድረግ፣ የተለያዩ ዶክመንቶችን በመከለስ ሲሆን በተጨማሪም ኦዲቱ በናሙና በተመረጡ በሐዋሳ፤ ሻሸመኔ፤ አዲስ አበባ በሚገኙ ኤጀንሲ ጽ/ቤቶች፤ ኢንርፕራዞችና ብድር አቅራቢ የፋይናንስ ተቋማት በአካል በመገኘት መጠይቅ በማድረግና የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ በተሰበሰቡት ማስረጃዎች ላይም አስፈላጊውን ትንተናና ንፅፅር (Analysis) በማካሄድ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process Description)

19. የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካትና የመንግሥት ድጋፍ አቅርቦት ማመቻቸት የማምረቻና የመሸጫ ክላስተር ማዕከላት በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ማዋልና ማስተዳደር፣ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት ማመቻቸት፣ የብድር አመላለስና የቁጠባ አሰባሰብን ማጠናከር፣ የሞዴል ኢንተርፕራይዞችን ፕሮፋይል በማደራጀትና ምርጥ ተሞክሯቸውን በመቀመር እንዲሰፉ ማድረግ፣ የኢንተርፕራይዞች አጠቃላይ መረጃዎች በዳታ ቤዝ በአንድ ማዕከል እንዲደራጅ ማድረግ፣ የአንድ ማዕከል አሰራር መመሪያዎችና ማኑዋሎችን በሥራ ላይ በትክክል እየዋሉ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል አስፈላጊ ሲሆን የማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል በሚል የአሰራር ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ የአሰራር ሥርዓቱ (Process Description) ስዕላዊ መግለጫ **በአባሪ 3** ይመልከቱ፡፡


# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

### የፋይናንስ ብድር አቅርቦት እና አመላለስ አፈጻጸምን በተመለከተ


20. የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራዞች የሚደረገውን የፋይናንስና ብድር አቅርቦት ድጋፍ በተመለከተ በአምስት ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ አካቶ ሊያቅድ ይገባል፡፡ ዕቅዱም በየበጀት ዓመቱ እየተመነዘረ በማቀድ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

21. የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በየዓመቱ ወደ ሥራ ለሚገቡ ለአዳዲስ ኢንተርፕራይዞች እና ነባር አንቀሳቃሾች የብድር አገልግሎት ለማመቻቸትና እንዲቀርብ ድጋፍ ለማድረግ በስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ አቅዷል፡፡ ነገር ግን የብድር ስርጭት ዕቅድ አፈጻጸምን ስንመለከት ከብድር ገንዘብ አቅርቦት አንጻር በዕቅዱ መሰረት ባይከናወንም አፈጻጸሙ በየጊዜው እየተሻሻለ መምጣቱ በ2004 (51%)፣ በ2005 (75%)፣ በ2006 (75%) እና በ2007 (86%) ታውቋል፡፡




| | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
|---|---|---|---|---|
| ዕቅድ | 1,937,883,975 | 3,643,326,309 | 6,740,655,534 | 7,578,297,639 |
| ክንውን | 1,015,096,274 | 2,725,090,809 | 5,063,860,859 | 6,541,880,959 |
| % | 51 | 75 | 75 | 86 |

22. ከብድር ተጠቃሚዎች ብዛት አንጻር ግን አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ በ2004 (14%)፣ 2005 (24%)፣ 2006 (16%) እና 2007 ዓ.ም (31%) ከዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ለማወቅ ተችላል፡፡




| | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
|---|---|---|---|---|
| ዕቅድ | 575,965 | 940,000 | 2,421,051 | 1,882,055 |
| ክንውን | 81,926 | 232,285 | 398,500 | 595,196 |
| % | 14 | 24 | 16 | 31 |

23. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመለከትናቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ኢንተርፕራይዞች በተሰበሰ መረጃ ለመገንዘብ እንደተቻለው የብደር መመሪያው የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ስራ ዕቅዱን/ የአዋጭነት ጥናቱን ለጽ/ቤት ባቀረቡ በ15 ቀናት ውስጥ ብድሩን እንዲያገኙ ይደረጋል ቢባልም በተጨባጭ ግን በተባለው ጊዜ ውስጥ እንደማይፈጸምላቸው በመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡

24. የተሰጠ ብድር አመላለስን በተመለከተ አበዳሪ ተቋሚት ላይ ወዝፍ ብድር እንዲኖርና ብሔራዊ ባንክ ያስቀመጠውን የ97% የብድር አመላለስ ምጣኔ መመሪያ እንዲሁም ኤጀንሲው ሲያቅድ የተሰራጨውን ብድር 100% መሰብሰብ እንዳለበት በግልጽ ቢያስቀምጥም ነገር ግን በየበጀት ዓመቱ የተሰራጨ ብድርን የማስመለስ አፈጻጸም ስንመለከት በ2004 (69%)፣ 2005 (64%)፣ 2006 (75%) እና 2007 ዓ.ም (88%) እንደሆነ ታውቋል፡፡

| በበጀት ዓመቱ ከተሰራጨው ብድር የተመለሰ ብድር (በብር) | | | |
|---|---|---|---|
| በጀት ዓመት | ዕቅድ | ክንውን | % |
| 2004 | 100% | 702,557,720 | 69 |
| 2005 | 100% | 1,761,423,221 | 64 |
| 2006 | 4,039,368,141 | 3,029,700,996 | 75 |
| 2007 | 4,293,870,905 | 3,797,180,684 | 88 |

25. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመለከተናቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት በተሰበሰበ መረጃ ለገንዘብ እንደተቻለው የብድር አቅርቦት ከኢንተርፕራይዝ ብዛት ጋር የማይመጣጠን መሆን፤ ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ብድር በተቀመጠላቸው የቆይታ ጊዜ ከፍለው ባለማጠናቀቃቸው ምክንያት የተጠራቀመ የብድር ውዝፍ እንዲከማች ማድረጉና የሚመለከታቸው የባለድርሻ አካለት ብድር ለመስጠቱ የሚተባበሩትን ያህል ማስመለስ ላይ ትብብራቸው አናሳ በመሆኑ በመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡

26. የፋይንናስ የብድር አቅርቦትና አፈጻጸምን በተመለከተ የኤጀንሲዉ ኃላፊዎች ተጠይቀው በፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት የብድር አቅርቦት እጥረት ምክንያት ጥያቄ ለሚያቀርቡትን ኢንተርፕራይዞች ሁሉ ማስተናገድ ባለመቻላቸውና መንግስት ትኩረት ለሰጠባቸው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ቅድሚያ እየተሰጠ የሚስተናገድ በመሆኑ ቢዝነስ ፕላኑ በቀረበ በ15 ቀን ውስጥ ሁሉንም ተበዳሪ ማስተናገድ ያልተቻለና ለብድር ጠያቂዎች ስለ አሰራሩ በግልፅ ባለማሳወቅ ክፍተት በመኖሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

27. ከብድር አቅርቦት አንጻር በዕቅዱ መሰረት ብዙ ችግር የሌለ ሲሆን ከተጠቃሚዎች ፍላጎት አንጻር ግን ዕቅዱን ማሳካት አለመቻሉን እና የሚሰጠው የብድር መጠንም የስራቸውን ባህሪ ያላገናዘበ መሆኑን በመረዳት የፋይናንስ አቅርቦቱ በኢንተርፕራይዞቹ የእድገት ደረጃ መሰረት እንዲሆን ጋይድ ላይን በማዘጋጀት ለክልሎች መላኩን፣ ነገር ግን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር አሁንም ክፍተቱ የሚታይ መሆኑና ለብደር የሚውል ገንዘብ እጥረት ዋነኛው ችግር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

28. በየከተማው የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት እና የአነስተኛ ብድር አቅራቢ ተቋማት ብድር የወሰዱ ኢንተርፕራይዞችን በወቅቱ እየተከታተለና እየደገፉ ወደ ውዝፍ እንዳይገቡ ከማድረግ አንጻር ውስንነት ያለ

በመሆኑ በዚህ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ውዝፍ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት በሁለቱም አካላት ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው እና ከዚህም በተጨማሪ የብድር አስመላሽ ኮሚቴ ተቋቁሞ በየወቅቱ ብድሩ እንዲመለስ የማድረግ ስራ በመስራት ለውጦች እየታዩ መጥተዋል ነገር ግን ቀደም ሲል በተፈጠሩ ችግሮች እስከሁንም ሙሉ በሙሉ መፍታት አለመቻሉን በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

29. ከዚህም ባሻገር በመውጫ ስብሰባና በተላከላቸው የረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ወቅት የብድር ስርጭት ከተጠቃሚዎች አንጻር ዝቅተኛ የሆነው ዕቅዱ አስቀድሞ ሲታቀድ ለኢንተርፕራይዞች እስከ 30,000 ብር ብድር ለማሰራጨት ነበር የታቀደው፡፡ ነገር ግን ዕቅዱ የነበረውንና የሚደርሱበትን የዕድገት ደረጃን ታሳቢ ያላደረገ በመሆኑ፣ በአሁኑ ሰዓት የኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕድገት እየጨመረ በመምጣቱና የሚፈልጉት የብድር መጠን በመጨመሩ አበዳሪ ተቋሚት ለአንድ ኢንተርፕራይዝ እስከ አንድ ሚሊዮን ብር ድረስ የሚያበድሩ በመሆኑ የገንዘብ ስርጭቱ በከፍተኛ ደረጃ በመጨሩ ካላቸው የገንዘብ መጠን ጋር ባለመጣጣሙ የተበዳሪዎች ቁጥር እንዲያንስ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

30. የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም የኦዲት ቡድኑ ግን ዕቅዱ ሲታቀድ በተገቢ ጥናት ላይ ተመስርቶ የብድር አቅርቦቱ ከብድር ተጠቃሚዎች ብዛትን ከግምት ውስጥ ያላስገባ ካሆነ እና የሚሰጡ ብድሮችም በወቅቱ እንዲመለሱ ካልተደረገ የኢንተርፕራይዞች ቀጣይነት ባለው መልክ የብድር አገልግሎት ማግኘት እንዳይችሉና ለብድር የሚሆን በቂ የገንዘብ አቅርቦት እንዳይኖር፣ የአበዳሪው ተቋም የገንዘብ አስተዳደር( liquidity) ጤናማ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የማደግ ሂደታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

## የብድር ዋስትና ፈንድ በተመለከተ

31. የብድር አሰጣጥ አገልግሎት ለማጠናከር እና በመደበኛ ባንኮች የተቀመጡትን የብድር ዋስትና/ማስያዣ (collateral) የማቅረብ አቅም ለሌላቸው ሥራቸውን ለመጀምር ወይም ለማስፋፋት የሚያስችል ብድር እንዲያገኙ ለማድረግ የብድር ዋስትና ፈንድ (Credit guarantee fund) በየክልል መንግስታት / በከተማ አስተዳደሮች ሊቋቋም ይገባል፡፡ ኢንተርፕራራይዞቹም የፈንዱን አላማ ምን

እንደሆነ እንዲያውቁት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ኤጀንሲውም ክልሎች ፈንዱን እንዲያቋቁሙ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡

32. በኤጀንሲው የአምስት ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር ዋስትና ፈንድ አሰራርና አተገባበር ጋይድ ላይን የብድር አገልግሎት ፈላጊ ኢንተርፕራይዞች ብድር ለማግኘት በመደበኛ ባንኮች የተቀመጡትን የብድር ዋስትና/ማስያዣ (collateral) የማቅረብ አቅም ስለሌላቸው ሥራቸውን ለመጀመር ወይም ለማስፋፋት የሚያስችል ብድር ለማግኘት ስለሚቸገሩ ይህን ችግራቸውን የሚፈታ የክልል መንግስታት በክልላቸው በየዓመቱ ሊሰጥ የታቀደውን የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን የብድር ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት በየዓመቱ የሚታደስ የብድር ዋስትና ፈንድ እንዲቋቋም ያደርጋሉ የሚል አቅጣጫ በዘርፉ ልማት ስትራቴጂ ተመልክቷል::

33. ይሁን እንጂ በናሙና በተመለከተናቸው ክልሎች ውስጥ ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በስተቀር የኦሮሚያ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልልች የብድር ዋስትና ፈንድ አለማቋቋማቸው ታውቋል፡፡ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በታዩ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት በሰጡት ምላሽና በተሰበሰ መረጃ ለመገንዘብ እንደተቻለው የከተማ መስተዳድሮች በራሳቸው ተነሳሽነት ለኢንተርፕራይዞች የብድር ዋስትና ሽፋን በመስጠት ብድሩ ቢመቻችም፤ ኢንተርፕራይዞች የተበደሩት ገንዘብ በማስመለስ ሂደት ላይ መንግስት ዋስ ሆኖልናል በሚል የተሳሰተ አስተሳሰብ ብድር ማስመለስ አለመቻሉን በመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡

34. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲዉ ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የብድር ዋስትና / ማስያዣ (collateral) የማቅረብ አቅም ለሌላቸው ሥራቸውን ለመጀምር ወይም ለማስፋፋት የሚያስችል ብድር ለማግኘት ለሚቸገሩ የዩኒቨርስቲና ቴክኒክና ሙያ ተመራቂዎች ይህን ችግራቸውን ለመፍታት ኤጀንሲው መመሪያ በማዘጋጀትና በማውረድ የብድር ዋስትና ፈንድ ተመድቦ አገልግሎት ላይ እንዲውል ክትትልና ድጋፍ ማድረጉን፣ የተወሰኑ ክልሎች ለብድር ዋስትና ፈንድ በጀት የመደቡ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት ወደ ትግበራ ከመግባት አንጻር በሁሉም ክልሎች ችግሩ መኖሩን ገልጸዋል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግም ክልሎችም ትኩረት ሰጥተው መንቀሳቀስ አልቻሉም፡፡ ሆኖም ለብድር ዋስትና ፈንድ የሚሆን ገንዘብ ተመድቦ ወደ ስራ ባይገባም በሁሉም ክልሎች

የከተማ አስተዳደሮች ለኢንተርፕራይዞች የብድር ዋስትና ሽፋን እየሰጡ የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

35. በሁሉም ክልሎች የብድር ዋስትና ፈንድ ወጥ በሆነ መልኩ አለመቋቋሙና ክልሎችም ትኩረት ሰጥተው አለመንቀሰቀሳቸው ሥራ ፈጠራን ለማበረታታ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በላይ የከተማ መስተዳድሮቹ በራሳቸው ተነሳሽነት ብቻ ገንዘቡን ለኢንተርፕራይዞቹ ማሰራጨቱ የመንግስት ሀብት እንዲባክን በር ሊከፍት ይችላል፡፡

## የድህረ ብድር ድጋፍና ክትትልን በተመለከተ

36. ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ገንዘብ ለታለመለት ዓለማና አቅርበውት በነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ተግባር ላይ ማዋላቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ ሊዘረጋ ይገባል፡፡

37. በ5 ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕይዞች ብድርና ቁጠባ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 008/2003 ዓ.ም ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አቅርበውት በነበረው የሥራ ዕቅድ መሠረት እየተገዙ መሆኑን፣ ደንበኞች ብድሩን በወሰዱ ከ15 እስከ 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ብድሩን በተባለው ተግባር ላይ ማዋላቸውን በአካል በመገኘት አበዳሪው የፋይናንስ አቅራቢ ተቋም እና የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ መደበኛ የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት ያልተቋረጠ ድጋፍና ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው ይገልጻል ::

38. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመለከተናቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ለመገንዘብ እንደተቻለው በስራቸው ትልቁ ችግር ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ብድር ለታለመለት ዓላማና አቅርበውት ለነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ተግባር እንደማያውሉት እና ይህም ስለመሆኑ የሚከታታል ስርዓት በኤጀንሲዎችም (ጽ/ቤቶች) ሆነ በአበዳሪ ተቋማት የተጠናከረ ክትትል የማይደረግ በመሆኑ አንዳንድ ኢንተርፕራዞች አቅርበውት ከነበረው የሥራ ዕቅድ ወጪ የተበደሩትን ገንዘብ ሌላ ስራ እያዋሉት በስራቸው ትልቁ ችግር እንደሆነባቸው ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ እና በመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡

39. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲዉ ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ቀደም ሲል በቅንጅት ከመስራት ይልቅ በተናጥል የመስራት ዝናባሌ የነበረና ሁሉም ብድር ለመስጠት እንጂ በቀረበው የስራ ዕቅድ መሰረት ተግባራዊ መደረጉንና በወቅቱም መመለስ የሚገባውን እንዲመለስ የማድረግ ስራ ላይ ክፍተት የነበረ ሲሆን አሁን ግን ኤጀንሲዎቹና አበዳሪ ተቋማት በጋራ የክትትል ስራ መስራት በመጀመራቸው ክፍተቱ እየቀነሰ እየመጣ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

40. የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት እና የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ መደበኛ የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት የድህረ ብድር ድጋፍና ክትትል ባለማደረጋቸው ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተቋቋሙበቱን አላማ እንዳይሳካ ከማድጉም በላይ የብድሩ ገንዘብ ለታለመት አላማ እንዳይውልና መመለሱንም አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

## የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት አቅርቦትን በተመለከተ

41. ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የስትራቴጂክ ዕቅድ በማውጣት በየዓመቱ በመመንዘር እየገነባ ለኢንተርፕራይዞቹ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

42. በ5 ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የማምረቻ፣ መሸጫና ገበያ ክላስተር ልማት አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 002/2003 ዓ.ም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በምርትና አገልግሎት ስራዎች ለመሰማራት እንዲችሉ ምቹ በሆነ ቦታዎች መሰረተ ልማት የተሟላለቸው፤ ህንጻዎችና ሼዶች በመገንባት በመጠነኛ ኪራይ ማቅረብን በዕቅድ ይዟል፡፡

43. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመለከተናቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ማዕከላት ግንባታቸው ተጠናቀው ሁለት ዓመት ቢያስቆጥርም ለኢንተርፕራይዞቹ እንዳልተላለፉ ከመስክ ጉብኝት ለመገንዘብ ተችላል፡፡

44. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በ5 ዓመታት ውስጥ ለመገንባት ከታቀዱት የሼድ፤ የህንፃና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት ሙሉ በሙሉ መሳካቱንና መሰረተ ልማት ሳይሟላላቸው ለብዙ ጊዜ የተቀመጡ የማምረቻና የመሸጫ ህንጻዎች እንዳሉ

ኤጀንሲው የሚያውቅና ይህንን ለሚመለከታቸው አካለት በማቅረብ እንዲፈታ ጥረት እያደረገ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

45. ከኤጀንሲው ዕቅድ አጻጸም ሲታይ ሼዶች ግንባታ በ2004፣ 2005፣ 2006 እና 2007 ዓ.ም (50%፣ 43%፣ 88% እና 69%) በቅደም ተከተል ሲሆን፣ የህንፃዎች ግንባታ ድግሞ በ2004፣ 2005፣ 2006 እና 2007 ዓ.ም (74%፣ 41%፣ 73% እና 37%) በቅደም ተከተል ሲሆን፣ አፈጻጸሙም ዝቅተኛ መሆኑን ከኤጀንሲው የዕቅድ ክንውን ዓመታዊ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችላል፡፡

46. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በ5 ዓመታት ውስጥ ለመገንባት ከታቀዱት የሼድ፣ የህንፃና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት ሙሉ በሙሉ መሳካቱንና ነገር ግን መሰረተ ልማት ሳይሟላላቸው ለብዙ ጊዜ የተቀመጡ የማምረቻና የመሸጫ ህንጻዎች እንዳሉ ኤጀንሲው የሚያውቅና ለሚመለከታቸው አካላት በማቅረብ እንዲፈታ ጥረት እያደረገ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

47. የሼዶችና የህንጻዎች ግንባታዎች በእቅዱ መሰረት ካልተሰሩና የተሰሩትም ለኢንተርፕራይዞቹ ካልተላለፉ መጀመሪያ ዕቅዱ በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀቱን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ሲሆን ተጠናቀው ስራ እንዲጀምሩ የሚፈለጉ ኢንተርፕራይዞች ሥራ እንዳይጀምሩ አድርጓቸዋል፡፡

### የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት መሰረተ ልማት የተሟላላቸው መሆኑንን በተመለከተ

48. ለጥቃቅንና አነስተና ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የከተሞችን ፕላን መሰረት በማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ስታንዳርድ ዲዛይን መሰረት በየማዕከላቱ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማት (መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ ሥልክ፣) ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ የጥበቃ ቤት አሟልተው ሊገነቡ ይገባል፡፡

49. ኤጀንሲው የማምረቻና መሸጫ ክላስተር ማዕከላት ወጥና በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጀውን ስታንዳርድ ዲዛይን መሠርት ያደረጉ፣ የየከተሞችን የእድገት ደረጃ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሆኖ መሰረተ ልማት (መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ ሥልክ)፣ የሰራተኞች ንፅህና መጠበቂያ ክፍሎች፣ የማእከሉ ማስተባበርያ ቢሮ፣ የጥሬ እቃ ማከማቻ መጋዘኖች፣ ምርት ማሳያና መሸጫ ክፍሎችን፣ ፓርኪንግ፣ መረጃ ማእከል፣ የስልጠና ቦታ፣ የምግብና መዝናኛ አገልግሎት፣ የደረቅና ፍሳሽ ማስወገጃ፣ ፓወር

ሃውስና የመሳሰሉትን በዋነኝነት የያዘና የስራ ዘርፎችን ባህርያት ታሳቢ ባደረገ መልኩ ማዘጋጀት እንዳለበት በስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ የተካተተ እና ለአተገባበሩም የማምረቻ፣ መሸጫና ገበያ ክላስተር ልማት አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 002/2003 ዓ.ም አዘጋጅቷል፡፡

50. ይሁን እንጂ በናሙና በተመለከተናቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ለመገንዘብ እንደተቻለው ከ2004 እስከ 2007 ዓ.ም ውስጥ ኤጀንሲው ተገንብተው ለማስተላለፍ ካቀዳው የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ውስጥ የሕንጻ ግንባታቸው ተጠናቆ ልዩ ልዩ መሰረተ ልማቶች (መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ ሥልክ)፣ ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ የጥበቃ ቤት በለመሟላቱ ለኢንተርፕራይዞቹ ያልተላለፉ መኖራቸውን፣ ለኢንተርፕራይዞቹ ተላልፈው ሥራ የተጀመረባቸው ማዕከላትም ቢሆኑ መሰረተ ልማቶቹ ሳይሟላላቸው እንደተላለፈላቸውና በዚህም ምክንያት እንደተቸገሩ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የተገነቡ የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የግንባታ ጥራት ችግር ያለባቸው መሆኑን በመስክ ጉብኝት ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

51. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የመሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው የማምረቻና የመሸጫ ህንጻዎች እንዳሉና ኤጀንሲው ችግሩን ለመቅፈር በተለይ የመብራት ችግር በሀገር አቀፍ ደረጃ ችግር ያለባቸውን በመለየት ስትሪንግ ኮሚቴ በማቋቋም በልዩ ሁኔታ ክፍያ ተከፍሎላቸው መብራት ያልገባላቸው አጠቃላይ 841 ህንፃዎች መኖራቸውን (በክልሎች ሲታይ ትግራይ 36፤ አማራ 37፤ ሱማሌ 6፤ ደቡብ 349፤ ድሬደዋ 2፤ ጋምቤላ 7፤ ኦሮሚያ 57 እና አዲስ አበባ 347 ሲሆኑ) በፌደራል ደረጃ በተቋቋመ ኮሚቴ መብራት እንዲገባላቸው ጥረት እየተደረገ ቢሆንም አሁንም ድረስ ችግሩን ሙሉ በሙሉ መፍታት አለመቻሉ እና ከግንባታ ጥራት ጋር በተያያዘ የግንባታ ቁጥጥር ስራውን የሚሰራው የክልሉ/ የከተማ አስተዳደሩ የቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ ሲሆን ኤጀንሲው በመስክ ክትትል በታዩ ክፍተቶች ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ ለሚመለከተው አካል እንደሚያሳውቅ ገልጸዋል፡፡

52. ከዚህም ባሻገር በመውጫ ስብሰባና በተላከላቸው ለረቂቅ ሪፖርት በሰጡት በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ግንባታ በዲዛይኑ መሰረት መሆኑንና ለተጠቃሚዎችም በመመሪያው መሰረት እየተላለፈ መሆኑንና የመሰረተ ልማት

አቅርቦት በተለይም የኃይል አቅርቦት ችግርን በፌደራል ደረጃ የሚፈታንትን ሁኔታ ድጋፍና ክትትል እንደሚደረግ፣ ግንባታውን ግን በዋናነት የሚያስተባብሩት ክልሎች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

53. ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው የተገነቡ ማዕከላት በመሰረተ ልማት ዕጥረት ምክንያት አገልግሎት መስጠት ያልጀመሩ የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት መኖራቸው የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋት የሚደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከመፍጠሩም በላይ ህንጻዎቹ አገልግሎት ሳይሰጡ እንዲበላሹ ያደርጋቸዋል፡፡ በተጨማሪም በተሟላ መልኩ የመሰረተ ልማት ሳይሟላላቸው ሥራ የጀመሩ ኢንተርፕራይዞች በተሠማሩበት የሥራ ዘርፍ ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

## ኢንተርፕራይዞች ደረጃ ዕድገት ሽግግርን በተመለከተ

54. አነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ የሚድጉበት ሁኔታ ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡ ኤጀንሲው የኢንተርፕራይዝ ደረጃ ሽግግር ከማድረጉ በፊት በየዕድገት ደረጃው በዓይነት፣ በቁጥርና በዘርፉ ብዛታቸው ለይቶ መረጃውን ሊይዝና በዚህም መሰረት በየአመቱ ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራዝነት የሚሸጋገሩትን መጠን በማቀድ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ የሽግግሩን ዕቅድ በተመለከተም በየደረጃው ለሚገኙ አስፈጻሚ አካላት ለተግባራዊነቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጣቸውና ተገቢውን ድርሻቸውን እንዲወጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

55. በ2003 ዓ.ም የወጣውን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ የድጋፍ ማዕቀፍና አፈፃፀም በመገምገም የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር መስፈርቶች ወጥተዋል፡፡ በወጡት መስፈርቶቹ መሰረት በሚኖሩ የኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃዎች እና የሚሰጡ የድጋፍ ማዕቀፎችን ለማመቻቸች ይረዳ ዘንድ የኢንተርፕራይዞችን በስድስት ዕድገት ደረጃ በመለየት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 004/2003 ዓ.ም ተዘጋጅቷል፡፡

56. ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በሀገር አቀፍ ደረጃ ካሉት ኢንተርፕራይዞች በየዓመቱ ከ1-2% ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት ለመሸጋገር ግብ የጣለ ቢሆንም በየደረጃው ያሉት ኢንተርፕራይዞች የእያንዳንዱ ብዛት ስንት እንደነበረ በግቡ ላይ በቁጥር ባለመጠቀሱ ዕቅዱ መሳካቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በናሙና በተመለከተናቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ

በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ከተከለሱ ዶክመንቶች በተገኘ መረጃ መሰረት ወደ ቀጣይ የዕድገት ደረጃዎች ለማሸጋገር የማሸጋገሪያ ስትራቴጂውን ያለመረዳትና የተረዱትንም ስራ ላይ ለመዋል እንደተቸገሩ በመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡

57. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በ2003 ዓ.ም ኤጀንሲው በአዲስ አደረጃጀት የተዋቀረና ያሉ ኢንተርፕራይዞች በዕድገት ደረጃ አለመለየታቸውን ገልጸዋል፡፡ የዕድገት ደረጃ ሽግግር መመሪያ ከክልል ጀምሮ እስከ አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ድረስ እንዲደርስ ክትትል የተደረገና በመመሪያው ላይ ለሁሉም አስፈፃሚ አካለት ስልጠና እንደተሰጠ ገልጸዋል፡፡ የየኢንተርፕራይዞቹ ዝርዝር መረጃ ለምን እንዳልተያዘ ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህንን ምላሽ ቢሰጡም አስፈጻሚ አካላት መመሪውን በግልጽ እንዳልተረዱት እና ለአፈጻጸም እንደተቸገሩ በመግለጻቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

58. ከዚህም ባሻገር በመውጫ ስብሰባና በተላከላቸው የረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ወቅት የዕድገት ደረጃ ሽግግር በጥቃቅንና በአነስተኛ ደረጀዎች እና ወደ ታዳጊ መካከለኛ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር ፕሮፋይል መረጃ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

59. ነገር ግን የቀረበልን መረጃ በተከለሰበት ጊዜ ከ2003 እስከ 2007 ዓ.ም ወደ ታደጊ መካከለኛ የተሸጋገሩ የኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ ዕቅድ አፈጻጸም እንጂ ከምን ያህል ኢንተርፕይዞች ምን ያህሉ እንደተሸጋገሩ፣ በየደረጃቸው ምን ያህል ኢንተርፕራይዞች እንዳሉ ዝርዝር መረጃው ባለመቅረቡ እና ያሉትን ጠቅላላ ኢንተርፕራይዞች ብዛት ባልተገለጸበት ሁኔታ በጥቅል ከ1-2% ካሉት አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ወደ ታዳጊ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ለማሸጋገር ማቀድ ዕቅዱም ሆነ አፈጻጸሙ ውጤታማ መሆኑን ለመለካት አዳጋች ያደርገዋል፡፡

60. ኤጀንሲው የኢንተርፕራይዞች በየዕድገት ደረጃው በዓይነት፤ በቁጥርና በዘርፉ ብዛታቸው አስቀድሞ ተይቶ መረጃው መዝግቦ ባልተያዘበት ሁኔታ ከምን ያህል ኢንተርፕርይዞች ውስጥ ምን ያህሉ ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ እንደተሸጋገሩ ማወቅን አዳጋች አድርጎታል፡፡

## ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ኢንተርፕራይዞችን በተመለከተ

61. ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የስራ መስኮች መስፈርት በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ ኢንተርፕራይዞች በመስፈርቱ መሰረት እየተመረጡ ወደየማዕከላቱ እንዲገቡ ሊደረግ ይገባል፡፡

62. በማምረቻ፣ በመሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚስተናገዱ ኢንተርፕራይዞች መምረጫ መመዘኛ መስፈርት እና በተለያየ እድገት ደረጃ ያሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ ምልመላ መከናወን እንዳለበት የሚረዳ የማምረቻ፣ መሸጫና ገበያ ክላስተር ልማት አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 002/2003 መዘጋጀቱ ታውቋል፡፡

63. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የሚገኙ 627 ሼዶች በህገ ወጥ መንገድ ለሶስተኛ ወገን የተከራዩ መሆኑን ከኤጀንሲው የዕቅድ ክንውን ዓመታዊ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

64. በተጨማሪም በናሙና በተመለከትናቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ማዕከላት የተዘጋጀውን መመልመያ መስፈርቶች ባልተከተለ መልኩ ወደ ማዕከላቱ የገቡ ግለሰቦችና ኢንተርፕራይዞች መኖራቸው፣ ወደ ማምረቻ ሕንፃ የሚገቡ የኢንተርፕራይዞቹ እንደ የሥራ ባህሪያቸው ሳይለዩ ወደ ህንጻው የገቡ በመሆኑ ኢንተርፕራይዞቹ በስራቸው ላይ ተጽኖ እንዳሳደረባቸውና በአንዳንድ ህንጻዎችም ላይ ጉዳት እየደረሰባቸው እንደሆነ በመስክ ጉብኝት ወቅት እና በናሙና ካነጋገርናቸው የኢንተርፕራይዝ ባለደረቦች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

65. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በ2003 ዓ.ም እና በ2004 ዓ.ም ለሶስተኛ ወገን የተከራዩ ማዕከላት እንደነበሩና ችግሩም በስፋት የተስተዋለ ሲሆን ይህን መሰረት በማድረግ ፌደራል ኤጀንሲ ለአመራሩ፣ ለባለሙያው ለአንቀሳቃሹ እና ለህብረተሰቡ ጭምር የግንዛቤ ስልጠና በመሰጠቱ ቀደም ሲል በህገወጥ መንገድ የተላለፉ የማምረቻና መሸጫ ቦታዎች በህብረተሰቡ ጥቆማ እንዲመለሱ ተደርጎ ለሚመለከታቸው አካላት በህጋዊ መንገድ የማስተላለፍ ስራ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ አንዳንድ ከተሞች

ላይ በየንዑስ ዘርፉ የተገነቡ ቢሆንም በዚያ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ጥቂት ከሆኑና ሌሎች ኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ቦታ ተቸግረው ካሉ ለነሱ የሚሆን ቦታ እከሚዘጋጅ ድረስ በጊዜያዊነት የመስጠት ስራ አልፎፎ አልፍ በአንዳንድ ከተሞች ላይ የሚታይ በመሆኑ ይህም የተደረገው በጊዜያዊነት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት ታስቦ የተደረገ መሆኑን፣ በህገወት መንገድ ለ3ኛ ወገን ከተላለፉት ውስጥ 117 ብቻ ሲቀሩ ሌሎቹ እንዲመለሱ የተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

66. የተዘጋጀውን የመመረጫ መስፈርት አለመጠቀም እና ማዕከላቱ ለተባለላቸው አላማ አለመዋላቸው የተገነቡ ህንጻዎችም ያገልግሎት ዕድሜ እንዲያጥርና ለማዕከላቱ ጥገና ተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ፣ አመቺ የሥራ አካባቢ እንዳይኖር የሚደርግ እና ለህገወጥ አሠራር ምቹ በር በመክፈት ማዕከላቱ የተገነቡበትን ዓላማ ከግብ እንዳያደርስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የፊትና የኋላ የገበያ ትስስርና ቁርኝት በተመለከተ

67. የየማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ውስጥ የሚገቡ ኢንተርፕራይዞች የሚመጋገቡ፣ የፊትና የኋላ የገበያ ትስስርና ቁርኝት ሊፈጥር የሚችሉበት ሁኔታ ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡ የፌዴራሉም ሆነ የክልል የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲዎች ይህ ትስስር መፈጠሩን ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡

68. ይሁን እንጂ በናሙና በተመለከተናቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ወደ ማዕከላት በሚገቡ ኢንተርፕራይዞቹ መካከል የፊትና የኋላ የገበያ ትስስር አለመፈጠሩን፣ ወደ ማምረቻ ሕንፃ ወይም ሼድ የሚገቡ ኢንተርፕራይዞቹ የሚያመርቱትን ምርት የመሸጫና የማሳያ ቦታ እንደ ማይመቻችላቸው በመስክ ጉብኝት ወቅትና በናሙና ለተመረጡ ኢንተርፕራይዝ አባላት ከቀረበው መጠይቅ ምላሽ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

69. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የህንፃዎች ዲዛይን ሲዘጋጅ ይህንን ችግር መመለስ በሚችል ደረጃ ተመመሳሳይና ተመጋጋቢ ስራ የሚያከናውኑ ኢንተርፕራይዞች መሰረት በማድረግ ከጥሬ ዕቃ ግብዓት እስከ ምርት ሽያጭ ድረስ በጋራ ተሳስረው መሰራት እንዲችሉ፣ የጋራ ችግሮቻቸውን በጋራ መፍታት ያለባቸው መሆኑን

ጭምር ታሳቢ በማድረግ የተገነቡ ቢሆንም ኢንተርፕራይዞችን በዚህ ደረጃ ሥራቸውን ለማከናወን ዝግጁ አለመሆን፣ በየከተሞችም ኢንተርፕራይዞችን የሚደግፉ አካላት በተገቢ ሁኔታ ባለመደገፋቸው አሰራሩን መዘርጋት አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

70. አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞቹ እርስ በእርሳቸው የፊትና የኋላ ትስስር አለመፈጠሩ፣ በገበያ፣ በቴክኖሎጂና በጋራ መሳሪያዎች ትስስር እንዳያደርጉ ከማድረጉም በሻገር የኢንዱስትሪውን እድገት እዝጋሚ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

## የማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት መጠቀሚያ የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ

71. ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚከፍሉት የዋጋ ተመን በክልል ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮዎች ተዘጋጅቶ ሊጸድቅ ይገባል፡፡ በጸደቀው ተመን መሰረት ኢንተርፕራይዞቹ የአገልግሎት ክፍያውን እንዲከፍሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

72. የማዕከላቱ የኪራይ ተመን ሲዘጋጅ የማምረቻ፣ የመሸጫ ማዕከላት የኪራይ ክፍያ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወደ ተሻለ እደገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የኪራይ መጠን ለኢንተርፕራይዞች ማዕከሉ ውስጥ ባላቸው ቆይታ የሚወሰን ሲሆን በመጀመሪያ ዓመት 25%፣ በሁለተኛ ዓመት 50%፣ በሶስተኛ ዓመት 75% እና በአራተኛና አምስተኛ ዓመት ሙሉ የኪራይ ተመኑ የኪራይ ዋጋ እንደሚከፍለና የየወሩ ኪራይ አሰባሰብ የመንግስትን የፋይናንስ ስርአት የተከተለ እንደሆነ የሚገልጽ የማምረቻ፣ መሸጫና ገበያ ክላስተር ልማት አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 002/2003 ተዘጋጅቷል፡፡

73. ይሁን እንጂ ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ ተመን ወጥነት ባለው መልኩ በየክልሎቹ ተመኑ ያልተዘጋጀ እና እና ክፍያውም በተሟላ ሁኔታ እንደማይሰበብና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ ማዕከላት ለመረዳት ተችሏል፡፡

74. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ የማምረቻና የመሸጫ ቦታ ተጠቃሚ ከሆነ ውል በመግባት ያለበት እና በመመሪያው መሰረት በመጀመሪያ ዓመት 25%፣ በሁለተኛ ዓመት 50%፣ በሶስተኛ ዓመት 75% እና 100%

የተቀመጠለትን ኪራይ መክፈል እንደሚገባው የወረዳ ሲሆን የሚከፈለውን ኪራይ የማውጣትና የመተመን ስራ እንደ የክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታና የከተሞቹን ደረጃ በማገናዘብ ክልሎች ተመኑን አውጥተው ማስተግበር ያለባቸው ቢሆንም አፈፃፀሙ ላይ ግን ክፍተት የሚታይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

75. የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የኪራይ ተመን ተዘጋጅቶ በተመኑ መሰረት በየጊዜው ካልተሰበሰበ የሚሰበሰበው ገንዘብ ለሌላ ስራ እንዳይውል ከማድረጉም በላይ ለህገወጥ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

## ኢንተርፕራይዞች በማዕከላቱ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜን በተመለከተ

76. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላቱ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ ጣሪያ ከ5 ዓመት አመት መብለጥ የለበትም፡፡ ኢንተርፕራይዞቹም ስለማዕከላቱ አጠቃቀም ውል መግባት ያለባቸው እና ጊዜያቸውን ሲጨርሱ ከማዕከላቱ ሊወጡ ይገባል፡፡ የኢንተርፕራዞቹ ቆይታ በውሉ መሠረት ተፈፃሚ ስለ መሆኑ በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

77. ወደ ታዳጊና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝነት የሚሸጋገሩ፤ በቂ የክህሎትና የፋይናንስ አቅም የፈጠሩና ተገቢውን ሥራ ለመስራት የሚያስችል የማምረቻ መሳሪያ ያላቸው፣ በግል ወይም በጋራ የራሳቸው የሆነ ወይም በኪራይ የመስሪያ ቦታ ያዘጋጁ፤ ከተደራጁ በኋላ ለ5 /አምስት/ ዓመታት ተከታታይ ድጋፍ ሲደረግላቸው የቆዩ፤ በሚደረገው ተከታታይ ክትትልና አስፈላጊ ድጋፍ ተደርጎላቸው ውጤታማ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት መውጣት አለባቸው ብሎ ሲያምን አምስት አመት ሳይሞላቸው ሊያስወጣቸው ይችላል የሚል የማምረቻ፣ መሸጫና ገበያ ክላስተር ልማት አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 002/2003 ዓ.ም ወጥቷል፡፡

78. ይሁን እንጂ በናሙና በተመለከተናቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ ማዕከላት ኢንተርፕራይዞች በማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላቱ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ ጣሪያ 5 ዓመት እንደሆነ መመሪያው ቢያዝም ከ5 ዓመት በላይ በማዕከላቱ ያስቆጠሩ ኢንተርፕራይዞች እንደሉ በመስክ ጉብኝት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

79. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በመመሪያው ላይ በ5 ዓመት ውስጥ ሙሉ ድጋፍ በመስጠት እንዲበቁ በማድረግ ወደ ባለሀብትነት በማሸጋገር ወደተዘጋጀላቸው ኢንዱስትሪ መንደር እንዲገቡ በማድረግ ለሌሎች የማስተላለፍ ስራ የሚሰራ መሆኑን ቢያስቀምጥም በዋናነት ለኢንተርፕራይዞች ወደ ማዕከሉ ከገቡ በኃላ ሙሉ ድጋፍ በመስጠት ማብቃት ባለመቻሉ እና በቅተውም ወደ ባለሃብትነት ለተሸጋገሩ ኢንተርፕራዞች በመመሪያው መሰረት አስቀድሞ የሚገቡበት የኢንዱስትሪ ቦታ የተዘጋጀላቸው ባለመሆኑ ካሉበት ቦታ ለማስወጣት አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

80. በመሆኑም ወደ ባለሃብትነት የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞችን ማዕከላቱን በተቀመተው ጊዜ ገደብ እንዲወጡ አለማድረግ ሌሎች አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን ለማስተናገድ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

## የማዕከል የቆይታ ጊዜ ጨርሰው ለሚወጡ ኢንተርፕራይዞች ስለሚደረግ ድጋፍ በተመለከተ

81. የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ውስጥ ተደራጅተው የገቡ ኢንተርፕራይዞች ከማዕከላቱ የመውጫ ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ ሄደው የሚገቡበት በኢንዱስትሪ ዞኖች እንደ ሥራው ባህሪያቸው ለኢንተርፕራዞቹ አስቀድሞ ቦታ መዘጋጀት አለበት፡፡

82. የማምረቻ፣ መሸጫና ገበያ ክላስተር ልማት አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 002/2003 ዓ.ም ከ5 ዓመት ቆይታ በኃላ ተመርቀው ሲወጡ ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ ከመውጣታቸው በፊት ሲወጡ ስለሚገጥማቸው የማምረቻና መሸጫ ቦታዎች አማራጮች በተከታታይ ግንዛቤ እንዲሰጣቸው በማድረግ አስቀድሞ በሚዘጋጅላቸው የኢንዱስትሪ ዞኖች ውስጥ፣ የማምረቻና መሸጫ ቦታዎች ወይም በተመጣጣኝ ዋጋ በሊዝ በሚወስዱት ቦታ ስራቸውን ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲቀጥሉ ድጋፍ ይደረግላቸዋል በማለት አስቀምጧል፡፡

83. ይሁን እንጂ በናሙና በተመለከትናቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በታዩ የቆይታ ጊዜቸውን ጨርሰው የሚወጡ ኢንተርፕራይዞች ከተመረቁ በኃላ ምንም ዓይነት ድጋፍ እንደማይደረግላቸውና ግማሾቹም ከማዕከላቱ ያልወጡ መሆኑን በመስክ ጉብኝት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

84. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የቆይታ ጊዜቸውን ጨርሰው የሚወጡና ወደ ባለሃብትነት የተሸጋገሩ አንተርፕራይዞች ተረክቦ አስፈላጊው ድጋፍ የሚያደርግ አካል ባለመኖሩ አሁንም ድረስ በጥቃቅንና አነስተኛ ስር ታቅፈው ያሉ ሲሆን የመስሪያ ቦታ ከተሞች በመነሻ ሊዝ ወደ መካከለኛ ባለሃብትነት ለተሸጋገሩ መስጠት የጀመሩ ሲሆን የፋይናንስ ድጋፍ በልማት ባንክ ይመቻችላቸዋል ቢባልም ችግሩ እስካሁን እልባት ባለማግኘቱ በወሰዱት ቦታ ላይ ግንባታ አከናውነው ወደስራ መግባትእንዳልቻሉ ገልጸዋል፡፡

85. ከዚህም ባሻገር በመውጫ ስብሰባና በተላከላቸው የረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ከማዕከላት የቆይታ ጊዜአቸውን ጨርሰው ለሚወጡ ኢንተርፕራይዞች ወደ ኢንዱስትሪ ዞን ወይንም በሌላ ቦታ ኢንቨስትመንታቸውን ለማሳዳግ ክልሎች በኩል የቦታ አቅርቦት ችግር አለመኖሩን ነገር ግን በልማት ባንክ በኩል ብድር ለማመቻቸት የሚቀርቡ መስፈርቶች የኢንተርፕራይዞችን አቅም ያላገናዘበ ችግር በመሆኑ በልማት ባንክ በኩል የአሰራር መመሪያ መስተካለል እንዳለበት በካውንስሉ ቀርቦ ውሳኔ ተሰጥቶበት በሂደት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

86. ከማዕከላት የቆይታ ጊዜአቸውን ጨርሰው ለሚወጡ ኢንተርፕራይዞች አስፈላጊ የሆነው ቅድመ ሁኔታ ካልተመቻቸላቸው ያጠራቀሙትን የተወሰነ ሀብት በኪራይና በሌላ ነገር በማዋል የፋይናነስ አቅማቸው እንዳይሻሻል በማድረግ ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ የሚደርጉትን ሽግግር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥርና መንግስት ያስቀመጠው የስራ ዕድል ፈጠራና ድህነት ቅነሳ ዕቅድ እንዳይሳካ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በሚመለከታቸው አካላት መካከል ያለ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ

87. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስና ብድር አቅርቦት እና የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ድጋፍ ላይ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ጽ/ቤት እና በየደረጃው ያሉ አመራሮች በቅንጅት ሊያቅዱና በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

88. በናሙና በታዩት የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች፣ በኦሮሚያ ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በናሙና ከታዮት የፋይናንስ ተቋማት እና ሌሎች

ባለድርሻ አካላት ጋር ኤጀንሲው ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ወጥነት በለው መልኩ የማይከነወን መሆኑን፣ በተለይም ብድር የማስመለስ ሂደት ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን እና በክልሎችና በከተማ መስተዳድሮች የሚገኙ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ልማት የሚመለከታቸው ፈጻሚና ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ የክትትልና የድጋፍ ሥርዓት ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም አተገባበር ላይ ወጥነት ባለው መልኩ አለመከናወኑን አለመዳበሩን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

89. ይህን በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ቅንጅታዊ አሰራር ከፌዴራል ጀምሮ የአደረጃጀት ጋይድ ላይን በማውረድ ተግባራዊ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን በተለይ 3ቱ አስፈጻሚ አካላት (ጥቃቅን፤ ቴክኒክና ሙያ እና ብደር አቅራቢ ተቋማት) ጋር ዕቅድ ከማዘጋጀት ጀምሮ አፈጻጸሙን የመገምገም ስራ እየተሰራ ያለ ሲሆን በአደረጃጀቱም የተለያዩ ንዑሳን ኮሚቴዎች ተቋቁመው ሥራ መጀመሩን ገልጸዋል፡፡

90. ወቅታዊና ወጥነት ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ወጥነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ የማይተገበር ከሆነ ብድር አቅራቢ የፋይናንስ ተቋማት ላይ ያልተሰበሰ ዕዳ እንዲጠራቀም፣ የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የግንባታ ጥራትና አጠቃቀም ላይ፣ እንዲሁም ከማዕከላት ተመርቀው የሚወጡት ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ የሚያደርጉት ሽግግርን አዳጋች ደርገዋል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

91. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የድጋፍ ማዕቀፎች አፈጻጸምን በተመለከተ የዘረጋው የአሠራር ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ሲገመገም የሚከተሉት ግድፈቶችና ጉድለቶች ተገኝተዋል፡፡

- የፋይናንስና ብድር አቅርቦት ቢኖርም የብድር ተጠቃሚዎች ብዛት ግን አነስተኛ መሆኑ፣
- በተከታታይ ዓመታት የተሰጠ ብድር ውስጥ ያልተመለሱ ብድሮች መኖራቸው፣
- የብድር ዋስትና ፈንድ ወጥ በሆነ መልኩ በየክልሎቹ አለመቋቋማቸው፣
- ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ገንዘብ ለታለመለት ዓለማና አቅርበውት በነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ተግባር ላይ ማዋላቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት አለመኖሩ፣
- ለማምረቻና ለመሸጫ ማዕከላት በዕቅድ ለመገንባት የሚያዙ ሼዶች እና ህንጻዎች አፈጻጸማቸው ዝቅትኛ መሆኑ፣
- የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ግንባታቸው ከተጠናቀቀ በኋላ  በተሟላ መልኩ የመሰረተ ልማት ያልተሟላላቸው መሆኑ፣
- የኢንተርፕራይዞች በየዕድገት ደረጃው በዓይነት፣ በቁጥርና በዘርፉ ብዛታቸው ለይቶ መረጃው በዕቅድና ግብ ላይ ያልተቀመጠ መሆኑ፣
- በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተብለው በተዘጋጁ ሼዶችና ሕንጻዎች የሚገቡ አካላት በተቀመጠው መስፈርት መሰረት አለመሆኑ፣
- የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞቹ እርስ በርሳቸው መካከል የፊትና የኋላ ትስስር ያልተፈጠረ መሆኑ፣
- የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ውስጥ የሚገቡ ኢንተርፕራይዞች የሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ ተመን በየክልልቹ ያልወጣ መሆኑ፣
- በማዕከል የቆይታ ጊዜ ጨርሰው መውጣት የሚገባቸው ኢንተርፕርይዞች ከማዕከላቱ እንዲወጡ የማይደረግ መሆኑ፣

- ከማዕከላት የቆይታ ጊዜአቸውን ጨርሰው ለሚወጡ ወደ ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ያደጉ አስፈላጊ የሆነው ቦታ እና ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች የማይመቻችላቸውና ድጋፍ የማይደረግላቸው መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ከአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ልማት ጋር ግንኙነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ያለው ቅንጅታዊ አሰራሩ ደካማ መሆኑ፣

92. ስለሆነም ከላይ የተገለጹት አፈጻጸም ላይ የታዩትን ጉድለቶችን ለማስወገድ ወይም ለማስተካከል ይረዳሉ ብለን ያስብናቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

93. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የድጋፍ ማዕቀፎች አፈጻጸምን በተመለከተ የዘረጋው የአሠራር ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- የፋይናንስና ብድር አቅርቦት በዕቅዱ መሰረት ሊከናወን እና የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የብድር ፍላጎትን ያገናዘበ የብድር አቅርቦት ሊኖር እና ሥራቸው አዋጪ እስከሆነ ድረስ ብድሩን የሚፈልጉ ኢንተርፕራይዞች ሁሉ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ በማመቻቸት የብድር ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞቹን ቁጥር ከፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በተለያየ ደረጃ ላይ ለሚገኙ (ለጀማሪ፣ ለታዳጊ እና ለበቁ) ጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለብድር አገልግሎት ብቁ ለመሆን የሚጠቀምባቸውን ቁጠባ አስቀድመው መቆጠብ ስለሚገባቸው ተገቢው ግንዛቤ ሊሰጣቸው እና በመመሪያው መሰረት የብድር ተጠቃሚ ከመሆናቸው አስቀድሞ ከሚበደሩት ከ15 - 40% ቁጠባ አስቀድመው በስድስት ወራት ውስጥ የቆጠቡ መሆናቸው እየተረጋገጠ ብድሩ ሊሰጣቸው እና ከተበደሩም በኋላ እየቆጠቡ መሆናቸው ተገቢው ክትትል በማድረግ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራዞች ሥራቸውን ለመጀመርም ሆነ ለማሻሻል የሚስፈልጋቸውን የፋይናንስ አቅም እንዲያገኙ የሚግዝ እና ለኢንተርፕራይዞቹ የብድር አሰጣጥ አገልግሎት ለማጠናከር የብድር ዋስትና ፈንድ (Credit guarantee fund) በክልል መንግስታት/ በከተማ አስተዳደሮች ሊቋቋም ይገባል፡፡ በብድር ዋስትና ተጠቅመው የተበደሩ አካላትም የተበደሩትን ገንዘብ በውሉ መሰረት እየከፈሉ መሆኑ ጥብቅ ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
- በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕርይዝነት ተደራጅተው የብድር ተጠቃሚ ለመሆን የሚያቀርቡት የሥራ ዕቅድ መሰረት የብድር ተጠቃሚ ከሆኑ በኋላ ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማና አቅርበውት በነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ተግባር ላይ ማዋላቸውን


የሚከታተልበትና የሚያረጋግጥበት ስርዓት ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት እና ሼዶች ግንባታ ለማካሄድ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ ሁኔታ የሚገነቡት ማዕከላት ብዛት በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊታቀድ ይገባል፡፡ የሚገነቡትም ማዕከላት እና ሼዶች በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ስታንዳርድ ዲዛይን መሰረት በማድረግ እና የየከተሞቹን ፕላን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መገንባት አለባቸው፡፡ ከማዕከላቱ ግንባታ ጋር አብረው መሟላት የሚገባቸው የመሰረተ ልማቶች (መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ ሥልክ)፣ ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ የመጸዳጃ ቤት፣ የጥበቃ ቤት የመሳሰሉት ተሟልተው ሊገነቡ ይገባል፡፡
- ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መምረጫ መስፈርት ተዘጋጅቶ በመስፈርቱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እና መስፈርቱ ያልተጣሰ ስለመሆኑም ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትል የሚደረግበት አሠራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ኢንተርፕራይዞቹ በማዕከላቱ ውስጥ ከአምስት አመት በላይ መቆየት እንደሌለባቸው ውል ሊገቡ እና በውሉ መሰረት ተፈጻሚ መሆኑ ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ሊያጋግጥ ይገባል፡፡ ኢንተርፕራያዞቹ በማዕከላቱ በሚቆዩበት የቆይታ ጊዜ መክፈል የሚገባቸው የኪራይ ተመን በየክልል በማውጣት በየወሩ እየከፈሉ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- ወደ ማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ውስጥ የሚገቡ ኢንተርፕራይዞች እርስ በርሳቸው የሚመጋገቡ፣ የፊትና የኋላ የገበያ ትስስርና ቁርኝት ሊፈጥር የሚችሉበት ሁኔታ ተመቻችቶላቸው ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝነት እንዲድጉ ተገቢው ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ ከማዕከላቱ የመውጫ ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ ወደመካከለኛ ኢንተፕራይዝነት ለሚሸጋገሩ ተቋማት በኢንዱስትሪ ዞኖች ውስጥም ሆነ በሌላ አመቺ በሆኑ ሥፍራዎች ለእያንዳንዱ ኢንተርፕራይዝ እንደ ሥራው ባህሪያቸው በመመሪያው መሰረት አስቀድሞ ቦታ ሊዘጋጅላቸው እና ተገቢው የፋይናንስ አቅርቦት የሚያገኙበት መንገድ ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ በየዕድገት ደረጃው በዓይነት፣ በቁጥርና በዘርፉ ብዛታቸው ለይቶ ዘመናዊ መረጃ አያያዝ ዘዴን በመጠቀም በተጠናከረ ሁኔታ ሊይዝ እና ይገባል፡፡
- ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስና ብድር አቅርቦት እና የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ድጋፍ ላይ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ጽ/ቤት እና በየደረጃው ያሉ አመራሮች በቅንጅት ለያዕቅዱና በዕቅዱም መሰረት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው የየክልሉና ከተማ መስተዳድሮች እና የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1. የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ አደረጃጀት



## አባሪ.2 የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

| **ኦዲት ጭብጥ** (Audit issue) | **የኦዲት መመዘኛ መስፈርት** (Evaluative Criteria) |
| --- | --- |
| 1. **የፋይናንስና ብድር አቅርቦት ድጋፍ ተግባር በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፡፡** | 1.1 ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስና ብድር አቅርቦት ድጋፍ በተመለከተ በአምስት ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊታቀድና በዛም መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.2 በአምስት ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የስራ ዘርፎች ላይ ለሚሰማሩ ኢንተርፕራይዝ ተበዳሪዎች ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ከሚበደሩት የብድር መጠን ቢያንስ 15 በመቶ ቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠባቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.3 የኤክስፖረት ምርት የሚያመርቱና በእድገት ተኮር ዘርፍ ከተሰማሩት ውጭያሉ ጀማሪ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ተበዳሪዎች ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ከሚበደሩት መጠን 25 በመቶ የቆጠቡ መሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.4 ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ብድር ተበዳሪ የሆኑ የጥቃቅንና አነስተና ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ብድር ከፍለው እስከሚያጠናቅቁ ጊዜ ድረስ የግዴታ መደበኛ ቁጠባ እየቆጠቡ መሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.5 የኢንቨስትመንት መሳሪያዎች ፕሮግራም ብድር ተጠቃሚዎች ለማሽነሪ ግዥ ከተገመተው ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ 40 በመቶ በቅድሚያ መቆጠባቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.6 ኢንተርፕራይዞች ብድር ሲጠይቁ በስራ ላይ ሊተገበሩና ውጤት ሊስገኝ የሚችል የአዋጭነት ጥናት አዘጋጅተው ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ |
| | 1.7 በኢንተርፕራይዞቹ የቀረበው የአዋጭነት ጥናት በሚከተለው አካል ተገምግሞ ሊያልፍ ይገባል፡፡ |
| | 1.8 የብድርና ቁጠባ ተቋማት በስርዓቱ ህጋዊ ሆነው በታክስ ከፋይነት ለተመዘገቡ ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ በመስጠት ሊበረታቱበት የሚያችል ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.9 የብድር አሰጣጥ አገልግሎት ለማጠናከር የብድር ዋስትና ፈንድ (Credit guarantee fund) በክልል መንግስታት/ በከተማ አስተዳደሮች ሊቋቋም ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 1.10 ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጥ ብድር የብድር ቆይታ ጊዜ 36 ወር ወይም 3 ዓመት በላይ መብለጥ የለበትም፡፡ |
| | 1.11 ኢንተርፕራይዞች የተበደሩትን ገንዘብ ለታለመለት ዓለማና አቅርበውት በነበረው የሥራ ዕቅድ (Business plan) መሰረት ተግባር ላይ ማዋላቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 1.12 ኢንተርፕራይዞች ብድር ሲጠይቁ ጀማሪዎቹ ዓማታዊ የሂሳብ መግለጫና ነባሮቹ ደግሞ (Audit) የተመረመረ ሰነድ ሊያቀረቡ ይገባል፡፡ |
| | 1.13 ኢንተርፕራይዞቹ በክላስተር ቆይታ ጊዜ ለቀጣይ ኢንቨስተመንት አገልግሎት የሚሆን ከገቢያቸው ቢያንስ 30% እንዲቆጥቡ የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ ክትትል ያደርጋል፡፡ |
| 2. **የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ድጋፍ አተገግባር ውጤታማ በሆነ የአሠራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን መገምገም፡፡** | 2.1 የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ድጋፍ በተመለከተ በአምስት ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊታቀድና በዛም መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.2 የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲዎች የወደፊት ዕድገትን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ለኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎችን በከተማዎች ማስተር ፕላን ውስጥ መካተታቸውን ሊያረጋግጥና የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ፕላን ኤጀንሲ ስም ተዘጋጅቶ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 2.3 ለጥቃቅንና አነስተና ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የከተሞችን ፕላን መሰረት በማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ስታንዳርድ ዲዛይን በተከለ መንገድ ለመሰረተ ልማት አቅርቦት አመቺ በሆኑ ቦታዎች ሊገነቡ ይገባል፡፡ |
| | 2.4 የገበያና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ምቹነት ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የሚመጋገቡ፣ ትስስርና ቁርኝት ሊፈጥር የሚችሉበት ቦታ በኢንዱስትሪ ዞን አካባቢ የተገነቡ መሆኑን የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲዎች ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡ |
| | 2.5 ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንደምርቶቻቸውና አገልግሎታቸው ዓይነት የገበያ ማዕከላት ቦታ የከተማው የመኖሪያ፣ የንግድ፣ የኢንዱስትሪ አካባቢዎች እና ለሸማቹ ለትራንስፖርት አመቺ የሆኑና ከከተማው የዕድገት ማዕከል ያልራቁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 2.6 ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የስራ መስኮች መስፈርት በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.7 ወደ ማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላት የሚገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚከፍሉት የዋጋ ተመን በክልል ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ተዘጋጅቶ ሊጸድቅና በዛም መሰረት ኢንተርፕራዞቹ የአገልግሎት ክፍያውን እንዲከፍሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2.8 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማምረቻ፣ መሸጫና የገበያ ማዕከላቱ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ ጣሪያ ከ5 ዓመት ሆኖ በሚገቡት ውል መሠረት ተፈፃሚ ስለ መሆኑ በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ኤጀንሲ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.9 በማዕከላቱ አካባቢ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የተለያዩ የአገልግሎት ስራዎች (መረጃ ማዕከል፣ ጤና ኬላ፣ የስብሰባ አደራሽ) የመሳሰሉት እንዲደራጁ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| 3. **የፋይናንስ፤ ብድር አቅርቦት፤ የማምረቻ እና የመሸጫ ማዕከላት የድጋፍ አተግባር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊያሠራ የሚያስችል ውጤታማ የአሠራር ሥርዓት ተዘረጋ መሆኑን መገምገም፡፡** | 1.1 ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስና ብድር አቅርቦትን እና የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ድጋፍ በተመለከተ በአምስት ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሲታቀድ የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ምክር ቤት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ሊታቀድና በዛም መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.2 ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስና ብድር አቅርቦት እና የብድር አመላለስ ሂደት ላይ የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲዎች እና በየደረጃው ያሉ አመራሮች በቅንጅት ሊያዕቅዱና በዛም መሰረት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | 1.3 ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ድጋፍ አተረባበር የፌዴራልና የክልል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ፤ የከተማ አስተዳደር (ማዘጋጃ ቤት ወይም አገልገሎት ጽ/ቤት)፤ የክልል ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ፤ በጋራ ሊያቅዱና በዕቅዱም መሰረት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 1.4 በየክልሉ ያሉ የአንስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ለኢንተርፕራይዞቹ የሚሰጠውን ብድር እና የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ድጋፍ አተረባበር የየሩብ ዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ እንዲደርስ ኤጀንሲው የተጠናከረ ግምገማ በማድረግ መረጃ ሊሰበስብ ይገባል፡፡ |

## አባሪ 3. የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process Description)

